የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአምስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፭
አዲስ አበባ ጥር ፩ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

15th Year No. 15
ADDIS ABABA 9th January, 2009

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፮፻፰/፪ሺ፩ ዓ.ም

የገቢ ግብር /ማሻሻያ/ አዋጅ ... ገጽ ፬ሺ፬፻፳፱

## አዋጅ ቁጥር ፮፻፰/፪ሺ፩

## የገቢ ግብር አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፮/፲፱፻፺፬ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፲፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የገቢ ግብር /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር ፮፻፰/፪ሺ፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. ማ ሻ ሻ ያ

የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፮/፲፱፻፺፬ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፣

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ /፲፫/ ውስጥ "የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን" ተብሎ የተጠቀሰው ተሰርዞ "የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን" በሚለው ተተክቷል።

፪/ ከአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ /፲፮/ ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች /፲፯/፣ /፲፰/፣ እና /፲፱/ ተጨምረዋል፣

CONTENTS

Proclamation No. 608/2008

Income Tax (Amendment) Proclamation Page 4429

## PROCLAMATION NO. 608/2008.

## A PROCLAMATION TO AMEND THE INCOME TAX PROCLAMATION

**WHEREAS,** it has become necessary to amend the Income Tax Proclamation N0. 286/2002;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (11) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Income Tax (Amendment) Proclamation No. 608/2008".

2. **Amendment**

The Income Tax Proclamation No. 286/2002 is hereby amended as follows:

1/ The reference to the "Federal Inland Revenue Authority" in sub-article (13) of Article 2 of the Proclamation is repealed and replaced by the "Ethiopian Revenues and Customs Authority".

2/ The following new sub-articles (17), (18) and (19) are added following sub article (16) of Article 2 of the Proclamation:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 4.40

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፲፯/ "በኤሌክትሮኒክስ መገናኛ የማስታወቂያና ክፍያ ዘዴ" ማለት በኮምፒውተ ራይዝድ የግንኙነት አውታር በመጠቀም የሚፈጸም የማስታወቂያና የክፍያ ሥርዓት ነው፣

፲፰/ "የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ" ማለት የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሣሪያ ወይም የሽያጭ ነቁጣ መሣሪያ ነው፣

፲፱/ "አቅራቢ" ማለት የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎችን ወይም በመሣሪያው ላይ ተጭኖ አገልግሎት የሚሰጥ ሶፍት ዌርን ወይም ሁለቱንም በአንድ ላይ የሚያቀርብ ሰው ነው።"

፫/ የአዋጁ አንቀጽ ፳፫ ንዑስ አንቀጽ /፲፩/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፲፩/ ተተክቷል፣

"፲፩/ ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለመወሰን ለንግድ ሥራው ቋሚ ንብረት የተደረገ የጥገና እና የማሻሻያ ትክክለኛ ወጪ እንዲቀነስ ይደረጋል። ወጪው ለእርጅና ቅናሽ መሰረት ከሆነው የዕቃ ሃያ ከመቶ በላይ ከሆነ ሙሉ በሙሉ በዕቃው የዘመኑ ቀሪ የመዝገብ ዋጋ ላይ ተደምሮ ወጪው በእርጅና ቅናሽ ደንብ መሠረት ይታሰባል።"

፬/ በአዋጁ አንቀጽ ፶፩ ንዑስ አንቀጽ /፫/፣ አንቀጽ ፶፫ ንዑስ አንቀፅ /፫/፣ አንቀጽ ፶፬ ንዑስ አንቀፅ /፫/፣ አንቀጽ ፷፮ ንዑስ አንቀፅ /፫/ እና አንቀጽ ፷፯ ንዑስ አንቀፅ /፪/ መጨረሻ ላይ የሚከተለው አዲስ ፓራግራፍ ተጨምሯል፣

"ግብር ከፋዩ ለግብር ባለሥልጣኑ መክፈል ያለበትን ግብር የግብር ባለሥልጣኑ በሚወክለው የፋይናንስ ተቋም በኩል ወይም በኤሌክትሮኒክስ የመገናኛ ዘዴ በማስታወቅ መክ ፈል ይችላል። ይህ አሠራር ሥራ ላይ የሚ ውልበት ጊዜ በኢትዮጵያ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በሚወጣ የሕዝብ ማስታ ወቂያ ይገለፃል።"

፭/ በአዋጁ አንቀጽ ፶፫ ንዑስ አንቀጽ /፫/ ውስጥ "ከወሩ የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ባሉት አሥር ቀናት ውስጥ" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "ከወሩ የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ባሉት ሠላሣ ቀናት ውስጥ" በሚለው ተተክቷል።



17/ 'electronic filing and payment system' means a method of E-filing and E-payment made by using a computerized net work;

18/ 'sales register machine' means a cash register machine or a point of sale machine;

19/ 'supplier' means a person who supplies sales register machines or software which gives service loaded on the cash register machine or supplies both in one to tax payers.

3/ Sub article (11) of Article 23 of the Proclamation is repealed and replaced by the following new sub article (11):

"11/ In determination of taxable business income deduction of the actual amount of maintenance and improvement expenses of a business asset is permitted. Where the actual amount of expense is in excess of 20% of the depreciation base of the asset, the whole expense shall be added to the book value of the asset at the year end to increase the depreciation base of the asset."

4/ The following new paragraph is inserted at the end of sub article (3) of Article 51, sub article (3) of Article 53, sub article (3) of Article 54, sub article (3) of Article 66 and sub article (2) of Article 67 of the Proclamation:

"The tax to be paid to the tax Authority by the tax payer can be made to financial institution delegated by the tax Authority or through electronically filing and payment system. The Ethiopian Revenue and Customs Authority by a public notice to be issued shall announce the commencement of such mode of payment."

5/ The phrase "Within ten days from the last day of each month" in sub article (3) of Article 53 of the Proclamation is repealed and replaced by "Within thirty days from the last day of each month."

፮/ ከአዋጁ አንቀጽ ፹፯ ንዑስ አንቀጽ /፪/ ተራ ፊደል /ሀ/ ቀጥሎ ተጓድሎ የነበረው የሚከተለው ተራ ፊደል /ለ/ ተጨምሯል፣

"ለ/ ብር ፳ሺ /ሃያ ሺህ ብር/።"

፯/ ከአዋጁ አንቀጽ ፺፩ ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች ፺፩ሀ፣ ፺፩ለ እና ፺፩ሐ ተጨምረዋል፣

"፺፩ሀ <u>የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አጠቃቀም ግዴታዎችን ባለመወጣት የሚጣል መቀጫ</u>

ማንኛውም በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የመጠቀም ግዴታ ያለበት ሰው፣

፩/ ዕውቅና ያልተሰጠው ወይም በባለሥልጣኑ ዘንድ ያልተመዘገበ መሣሪያ ወይም የሽያጭ ነቁጣ ሶፍትዌር ሲጠቀም ከተደረሰበት ለተጠቀመበት ለእያንዳንዱ መሣሪያ ብር ፶ሺ ይቀጣል፣

፪/ መሣሪያው በጥገና ላይ ባለበት ጊዜ ካልሆነ በስተቀር በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ከታተመ ደረሰኝ ውጪ በሌላ ማናቸውም ዓይነት ደረሰኝ ወይም ያለደረሰኝ ግብይት ካከናወነ ብር ፶ሺ ይቀጣል፣

፫/ በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ላይ ጉዳት ያደረሰ ወይም የፊሲካል ማስታወሻው እንዲቀየር ያደረገ ወይም ጉዳት ለማድረስ ወይም ማስታወሻውን ለመቀየር ሙከራ ያደረገ ከሆነ ብር ፻ሺ ይቀጣል፣

፬/ የግብር ባለሥልጣን ሠራተኛ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያን ሥርዓት ኦዲት እንዳያደርግ መሰናክል ከፈጠረ ወይም በመሣሪያው ላይ በዓመት አንድ ጊዜ በአገልግሎት ማዕከል የቴክኒክ ምርመራ ካላስደረገ ብር ፳፭ሺ ይቀጣል፣

፭/ በንግድ ሥራው ለሚጠቀምበት የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ከአገልግሎት ማዕከል ጋር ውል ካልፈጸመ ወይም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያውን ያውን ከተርሚናል ጋር ሳያያይዝ ከተጠቀመ ወይም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው የምርመራ መዝገብ ከመሣሪያው ጎን እንዲቀመጥ ካላደረገ ወይም በሽያጭ መመዝገቢያ የተመዘገቡ ዕቃዎች ተመላሽ መደረጋቸው ወይም ደንበኛው የተመላሽ ጥያቄ ማቅረቡ በተመላሽ መዝገብ ላይ በትክክል መመዝገቡ ሳይረጋገጥ የተመላሽ ደረሰኝ ከሰጠ ብር ፳፭ሺ ይቀጣል፣



6/ The missing text of paragraph (b) of sub article (2) of Article 87 of the Amharic version is inserted.

7/ The following new sub articles 91b and 91c are added after Article 91 of the Proclamation:

"91a. **<u>Penalties for Failure to Meet Requirements of the use of sales Register Machines</u>**

Any person who has the obligation to use sales register machine shall be liable for a penalty of :

1/ Birr 50,000 if found using sales register machine or point of sales machine software not accredited or registered by the tax Authority;

2/ Birr 50,000 for carrying out transactions without receipt or invoice or for using any other receipt not generated by a sales register machine except at the time the machine is under repair;

3/ Birr 100,000 if caused damage to or change of fiscal memory or attempts to cause damage to or change of fiscal memory;

4/ Birr 25,000 for obstructing inspection of the audit system of a sales register machine by officer of the Tax Authority or for failure to have annual machine inspections performed by a service center;

5/ Birr 25,000 for not having a valid service contract with an authorized service center for a sales register machine in use, or for using the sales register machine without connecting to the terminal, or for not keeping the inspection booklet besides the sales register machine, or for issuing refund receipts without properly recording the return of goods or customers' request for refund in the refund book;

፮/ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው በስርቆት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት በመሆኑ አገልግሎት መስጠት ሲያቋርጥ በሦስት ቀናት ጊዜ ውስጥ ወይም በሌላ ማናቸውም ምክንያት የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው ብልሽት ባጋጠመው በሁለት ሰዓት ውስጥ ለአገልግሎት ማዕከሉና ለግብር ባለሥልጣኑ ካላስታወቀ ብር ፲ሺ /አሥር ሺ ብር/ ይቀጣል፣

፯/ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የሚቀመጥበትን የንግድ ቦታ ትክክለኛ አድራሻ ለግብር ባለሥልጣኑ ያላስታወቀ እንደሆነ ብር ፶ሺ /ሃምሣ ሺ ብር/ ይቀጣል

፰/ የአድራሻ ወይም የስም ለውጥ ሲያደረግ ወይም የንግድ ሥራውን የሚያቋርጥ ሲሆን ከሦስት ቀናት አስቀድሞ ለአገልግሎት ማዕከሉና ለግብር ባለሥልጣኑ ያላስታወቀ እንደሆነ ብር ፳፭ሺ ይቀጣል፣

፱/ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው ጥቅም ላይ በሚውልበት የንግድ ሥራ ቦታው፣

ሀ/ የተጠቃሚውን ስም፣ የንግድ ስም፣ የንግዱ ሥራ የሚካሄድበትን አድራሻ፣ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር፣ የሽያጭ መመዝገ ቢያ መሣሪያውን የዕውቅና እና የመጠቀሚያ ፈቃድ ቁጥር፣

ለ/ /የሽያጭ ሠራተኞች መሣሪያው የተበላሸ ከሆነ በግብር ባለሥልጣኑ ፈቃድ የታተመ ተከታታይ ቁጥር ያለው ደረሰኝ ለደንበኛው የመስጠት ግዴታ አለባቸው/ የሚል ማስታወቂያ፣ እና

ሐ/ /ደረሰኝ የማይሰጥ ከሆነ አይከፈሉ/ የሚልጽሁፍ ያለበት ማስታወቂያ፣

በግልጽና በሚታይ ቦታ ለጥፎ ካልተገኘ ብር ፲ሺ ይቀጣል፣

ሥራ ላይ የዋለውን የሽያጭ ነቁጣ ሶፍትዌር የግብር ባለሥልጣኑ ዕውቅና ባልሰጠው ሰው እንዲቀየር ወይም እንዲሻሻል ካደረገ ብር ፴ሺ ይቀጣል።

6/ Birr 10,000 for failure to inform the Tax Authority and the machine service center within three days of the termination of a sales register machine use due to theft or irreparable damage, or within two hours for failure to report machine malfunction due to any other causes;

7/ Birr 50,000 for failure to notify the Tax Authority the correct place of business the sales register machine is in use;

8/ Birr 25,000 for failure to notify the Tax Authority change of name or address or for failure to notify the Tax Authority and Service Center three days in advance in cases of termination of business;

9/ Birr 10,000 for failure to put a conspicuous notice containing one or all the following information at a place where the machine is installed:

a) name of the machine user, trade name, location of trade, taxpayers' identification number, accreditation and permit numbers for the sales register machine;

b) text stating that "in case of machine failure sales personnel must issue manual receipts authorized by the Tax Authority";

c) text that reads "Do not pay if a receipt is not issued";

10/ Birr 30,000 for changing or improving a point of sales machine software by a person not accredited by the Tax Authority.

## ፺፩ለ. <u>የአቅራቢነት ግዴታዎችን ባለመወጣት የሚጣል መቀጫ</u>

ማንኛውም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ወይም ሶፍትዌር አቅራቢነት ዕውቅናና ፈቃድ የተሰጠው ሰው፣

፩/ የንግድ ሥራውን የአድራሻ ለውጥ ለግብር ባለሥልጣኑ ካላስታወቅ ብር ፩፻ሺ ይቀጣል፣

፪/ በግብር ባለሥልጣኑ ዕውቅና ያልተሰጠውን የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ለገበያ ካዋለ ብር ፭፻ሺ ይቀጣል፣

፫/ ለእያንዳንዱ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ምዝገባ ከግብር ባለሥልጣኑ የመሣሪያ መለያ ቁጥር ካልወሰደ ወይም የወሰደውን የመሣሪያ መለያ ቁጥር ለእይታ በሚያመች ቦታ በመሣሪያው ላይ ካለጠፈ ብር ፶ሺ ይቀጣል፤

፬/ በሥራ ላይ ባሉ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ላይ የሚያደርገውን ማናቸውም ለውጥ ለግብር ባለሥልጣኑ በቅድሚያ ካላስታወቀ ወይም ስለመሣሪያው አጠቃቀም በሚያብራራው የአጠቃቀም መመሪያ ውስጥ ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ካስገባ ወይም ትክክለኛውን መረጃ ከቀነሰ ብር ፩፻ሺ ይቀጣል፤

፭/ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች በመሠረቃቸው ወይም ሊጠገኑ በማይቻልበት ሁኔታ በአደጋ ምክንያት ብልሽት የደረሰባቸው መሆኑን አስታውቀው እንዲተኩላቸው ለሚጠይቁ የአገልግሎት ማዕከላት በሦስት ቀናት ውስጥ ለማቅረብ አለመቻሉን ለግብር ባለሥልጣኑ አስቀድሞ ካላስታወቀ ብር ፶ሺ ይቀጣል፤

፮/ ውል ስለተዋዋላቸው የአገልግሎት ማዕከላት መረጃ ካልያዘ ወይም ውላቸውን ስላቋረጡ ወይም አዲስ ስለተዋዋላቸው የአገልግሎት ማዕከላት ለግብር ባለሥልጣኑ ካላስታወቀ ብር ፶ሺ ይቀጣል።

## 91b. <u>Penalties for Failure to Observe Supplier's obligations</u>

Any person who is accredited and permitted for the supply of sales register machine or soft ware shall be liable for a penalty of:

1/ Birr 100,000 for failure to notify change of business address to the Tax Authority;

2/ Birr 500,000 for selling a sales register machine not accredited by the Tax Authority;

3/ Birr 50,000for failure to get a machine registration code for each sales register machine from the Tax Authority or for not affixing the machine code stickers on a visible part of the machine;

4/ Birr 100,000 for failure to notify to the Tax Authority in advance any change made to the sales register machine in use or for inserting or adding incorrect information or for omitting the correct information from the manual that guides the use of sales register machine;

5/ Birr 50,000 for failure to notify the Tax Authority in advance or for not being able to replace, within three days of the request made by a service center, sales register machine lost due to theft or sustained irreparable damage;

6/ Birr 50,000 for failure to keep information about service centers with which it has signed agreements or for failure to notify the Tax Authority about contracts terminated or newly entered agreements with service centers.

፺፩ሐ. የአገልግሎት ማዕከል ግዴታዎችን ባለመወጣት የሚጣል መቀጫ ማናቸውም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች የአገልግሎት ማዕከል፣

፩/ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የፊሲካል ማስታወሻ በተተካ በሁለት ቀናት ውስጥ ለግብር ባለሥልጣኑ ካላስታወቀ ብር ፳ሺ. ይቀጣል፤

፪/ ውል የገባባቸውን የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች በዓመት አንድ ጊዜ የቴክኒክ ምርመራ ካላደረገ ብር ፳ሺ. ይቀጣል፤

፫/ አቅራቢው ዕውቅና ሳይሰጠውና በግብር ባለሥልጣኑ ዘንድ ሳይመዘገብ በሥራ ላሠማራው ለእያንዳንዱ ሠራተኛ ብር ፶ሺ. ይቀጣል።

፰/ ከአዋጁ አንቀጽ ፺፯ ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ አንቀጽ ፺፯ሀ፣ ፺፯ለ እና ፺፯ሐ ተጨምረዋል፤

"፺፯ሀ. **የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አጠቃቀምን በሚመለከት ስለሚፈጸም ጥፋት**

ማንኛውም በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የመጠቀም ግዴታ ያለበት ሰው፣

፩/ በግብር ባለሥልጣኑ ዕውቅና ያልተሰጠው ወይም ያልተመዘገበ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ከተጠቀመ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፤

፪/ መሣሪያው በጥገና ላይ ባለበት ጊዜ ካልሆነ በስተቀር በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ከታተመ ደረሰኝ ወጪ ወይም ያለደረሰኝ ግብይት ካከናወነ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል፤

91c. Penalties for Failure to Observe Sales Register Machine Service Center's Obligations Any Sales Register Machine Service Center shall be liable for a penalty

1/ Birr 20,000 for failure to report to the Tax Authority within two days of change of the fiscal memory of a sales register machine;

2/ Birr 20,000 for failure to perform annual technical inspections on sales register machines that are under contract;

3/ Birr 50,000 for deploying every person not certified by the supplier and not registered by the Tax Authority."

8/ After Article 97 of the Proclamation the following new Articles 97a, 97b and 97c are added:

"97a. **Violations of the Requirements of the use of Sales Register Machines**

Any person who has the obligation to use sales register machine;

1/ commits an offence if found using a sales register machine not accredited or registered by the Tax Authority and shall, upon conviction, be punished with imprisonment for a term of not less than one year and not more than two years;

2/ except at the time the sales machine is under repair, commits an offence if carried out transactions without receipt or invoice or used any other receipt not generated by a sales machine and shall, upon conviction, be punished with imprisonment for a term of not less that one year and not more than two years;

፫/ በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው የፊሲካል ማስታወሻ ላይ ጉዳት ያደረሰ ወይም የፊሲካል ማስታወሻው እንዲቀየር ያደረገ ወይም ጉዳት ለማድረስ ወይም ማስታወሻውን ለመቀየር ሙከራ ያደረገ ከሆነ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከሦስት ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል።

፬/ የግብር ባለሥልጣኑ ሠራተኛ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያውን ሥርዓት ኦዲት እንዳያደርግ መሰናክል የፈጠረ ወይም በመሣሪያው ላይ በዓመት አንድ ጊዜ በአገልግሎት ማዕከል የቴክኒክ ምርመራ ያላስደረገ ከሆነ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከስድስት ወር በማያንስና ከአንድ ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል።

፭/ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያው የሚገኝበትን የንግድ ቦታ ትክክለኛ አድራሻ ለግብር ባለሥልጣኑ ያላስታወቀ እንደሆነ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከስድስት ወር በማያንስና ከአንድ ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል።

፺፯ለ. <u>በአቅራቢዎች የሚፈጸሙ ጥፋቶች</u>

ማንኛውም በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ወይም ሶፍትዌር አቅራቢነት ዕውቅናና ፈቃድ የተሰጠው ሰው፤

፩/ የንግድ ሥራውን የአድራሻ ለውጥ ለግብር ባለሥልጣኑ ካላስታወቀ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል።

፪/ በግብር ባለሥልጣኑ ዕውቅና ያልተሰጠውን መሣሪያ ለገበያ ካዋለ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከሦስት ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል።

3/ commits an offence if caused damage or change to the fiscal memory of a sales register machine or attempts to cause damage or change to the fiscal memory and shall, upon conviction, be punished with imprisonment for a term of not less than three years and not more than five years;

4/ commits an offence if obstructed inspection of the audit system of a sales register machine by officer of the Tax Authority, or if failed to have annual machine inspections performed by a service center and shall, upon conviction, be punished with imprisonment for a term of not less than six months and not more than one year;

5/ commits an offence if failed to notify to the Tax Authority the correct business address where a sales register machine is in use and shall, upon conviction, be punished with imprisonment for a term of not less than six months and not more than one year.

97b. <u>Offences by Suppliers</u>

Any person who is accredited and registered to supply sales register machines:

1/ commits an offence if failed to report to the Tax Authority a change of business address and shall, upon conviction, be punished with imprisonment for a term of not less than one year and not more than two years;

2/ commits an offence if sold a sales register machine not accredited by the Tax Authority and shall, upon conviction, be punished with imprisonment for a term of not less that three years and not more than five years;

፫/ በሥራ ላይ ባሉ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ላይ የሚያደርገውን ማናቸውም ለውጥ ለታክስ ባለሥልጣኑ በቅድሚያ ካላስታወቀ ወይም በመሣሪያው የአጠቃቀም መመሪያ ውስጥ ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ካስገባ ወይም ትክክለኛውን መረጃ ከቀነሰ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከሦስት ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል።

.. <u>በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች የአገልግሎት ማዕከልና ሠራተኞች የሚፈጸሙ ጥፋቶች</u>

፩/ ማናቸውም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች የአገልግሎት ማዕከል አቅራቢው ዕውቅና ያልሰጠውንና በባለሥልጣኑ ዘንድ ያልተመዘገበ ሠራተኛ በሥራ ላይ አሰማርቶ ከተገኘ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሦስት አመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል።

፪/ ማናቸውም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች የአገልግሎት ማዕከል ሠራተኛ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያን ያለአገልግሎት ማዕከሉና የግብር ባለሥልጣኑ ዕውቅና ከፈታታ ወይም ከገጣጠመ ወይም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ሳይበላሽ ሆን ብሎ እሽጉን ካነሳ ወይም አካሉን ከቀየረ ወይም እነዚህን የመሳሰሉ አድርጎቶች ከፈጸመ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር ፭ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሦስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል።"

፱/ የአዋጁ አንቀጽ ፺፱ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፺፱ተተክቷል፤

"፺፱. <u>በግብር ባለሥልጣኑ ሠራተኞች የሚፈፀሙ ጥፋቶች</u>

፩/ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ለማስፈፀም በግብር ባለሥልጣን የተቀጠረ ማንኛውም ሰው፤

3/ commits an offence if failed to notify the Tax Authority in advance any change made to the sales register machine in use, or if inserted incorrect information to or omitted the correct information from the manual that guides the use of sales register machine and shall, upon conviction, be punished with imprisonment for a term of not less than three years and not more than five years.;

97c.<u>Offences by Sales Register Machine Service Centers and their Personnel</u>

1/ Any sales register machine service center commits an offence if deployed a service personnel that is not certified by the supplier and not registered by the Tax Authority and shall, upon conviction, be punished with imprisonment for a term of not less than one year and not more than three years.

2/ Any personnel of a sales register machine service center commits an offence if, without the knowledge of the service center and the Tax Authority, dismantle or assemble a sales register machine, or if deliberately removed the seals on a sales register machine or changed parts of a sales register machine not reported to have any break down, or if committed any similar act and shall, upon conviction, be punished with a fine of not more than Birr 5,000 and imprisonment for a term of not less than one year and not more than three years."

9/ Article 99 of the Proclamation is repealed and replaced by the following new Article 99

"99. <u>Offences by Tax Authority Employee</u>

1/ Any person employed by the Tax Authority for enforcing the provisions of this Proclamation who:

ሀ/ በሕግ መሠረት ሊያገኘው ከሚገባው ክፍያ ወይም ሽልማት ውጪ ከተቀጠረበት ተግባር ጋር በተያያዘ በቀጥታ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የገንዘብ ወይም ሌላ ዓይነት ክፍያ ወይም ስጦታ እንዲደረግለት የጠየቀ ወይም የተቀበለ ወይም ለክፍያው ወይም ለስጦታው ተስፋ ወይም መያገር የጠየቀ ወይም የተቀበለ እንደሆነ፣

ለ/ ከግብር በሚገኘው ገቢ ላይ ማጭበርበር ወይም ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም ከተሰጠው ኃላፊነት መልካም አፈጻጸም ጋር የሚቃረን ተግባር ለመፈፀም፣ ማድረግ የሚገባውን ከማድረግ ለመታቀብ፣ ተገቢ ያልሆነን ነገር ለመፍቀድ፣ በግብር ላይ የሚፈፀምን የማጭበርበር ተግባር ለመደበቅ ወይም በሚስጥር ለመተግበር ውል የገባ ወይም በሚገባው ማናቸውም ውል ውስጥ በዚህ ተግባር መተባበሩን የሚያሳይ ስምምነት የሰጠ እንደሆነ ወይም፣

ሐ/ በዚህ አዋጅ ለግብር ባለሥልጣኑ ከተሰጠው ሥልጣን በላይ የሠራ ወይም በተሰጠው ሥልጣን ያለአግባብ የተጠቀመ እንደሆነ፣

ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር ፶ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከ፲ ዓመት በማያንስ ከ፳ ዓመት በማይ በልጥ እሥራት ይቀጣል።

፪/ የግብር ባለሥልጣኑ ሠራተኛ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች አጠቃቀም ደንብና መመሪያዎችን በመተላለፍ፣

ሀ/ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የፈታ ወይም የገጣጠመ ወይም የአገልግሎት ማዕከል ሠራተኛ በሌለበት ሥራ ላይ እንዲውል የፈቀደ ወይም የመሣሪያውን መለያ ቁጥር ያቀያየረ እንደሆነ፣ ወይም

ለ/ በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ተጠቃሚው ወይም በአገልግሎት ማዕከሉ ወይም በሠራተኛው ወይም በአቅራቢው የተፈጸመን ማናቸውንም ሕገ ወጥ አድራጎት እያወቀ ወይም በቸልተኝነት በ፳፬ ሰዓት ጊዜ ውስጥ ለግብር ባለሥልጣኑ ሪፖርት ያላደረገ እንደሆነ፤ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር ፭ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሦስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል።

a) in connection with any of his duties, directly or indirectly asks for or receives a payment or reward, whether pecuniary or other wise, or promise or security for that payment or reward, not being a payment or reward to which he is lawfully entitled to receive;

b) enters into or acquiesces in an agreement to do or to abstain from doing any thing, or to permit, conceal or connive at any act where by the tax revenue id defrauded or which is contrary to the provisions of this Proclamation or to the proper execution his duty; or

c) exceeds the power conferred upon the Tax Authority or misuses such authority;

commits an offence and shall, up on conviction, be punished with a fine of not more than Birr 50,000 and imprisonment for a term of not less than 10 years and not more than 20 years.

2/ Any employee of the Tax Authority who, in violation of the rules and procedures of the use of sales register machines:

a) dismantles or assembles a sales register machine or approves its utilization without the presence of a service personnel or changes the machine registration code; or

b) knowingly or negligently fails to report to the Tax Authority, within 24 hours, offences committed by the user, service center or its personnel or supplier of a sales register machine;

commits an offence and shall, upon conviction, be punished with a fine of not more than Birr 5,000 and imprisonment for a term of not less than one year and not more than three years.

፫/ የግብር ባለሥልጣኑ ሠራተኛ ያለ በቂ ምክንያት ጉዳይን በማጓተት በግብር ከፋይ ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት በፍትሐብሔር ያለበት ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል።"

፲/ የአዋጁ አንቀጽ ፩፻፲፪ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ተተክቷል፤

"፩/ የይግባኝ ጉባኤ የሰጠው ውሳኔ በሕግ ረገድ ስህተት ነው በማለት ያልተስማማ ማንኛውም ተከራካሪ ወገን የይግባኝ ጉባኤው የጽሑፍ ውሳኔ በደረሰው በ፴ ቀናት ውስጥ ሥልጣን ላለው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል።"

፲፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፩፻፲፪ ንዑስ አንቀጽ /፬/ ተሽሯል።

፲፪/ የአዋጁ አንቀጽ ፩፻፲፬ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ተተክቷል፤

"፩/ በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አባላት የንግዱን ህብረተሰብ ተወካዮች ጨምሮ በሕዝብ ዘንድ ባላቸው ታዋቂነትና ታማኝነት፣ ባላቸው ጠቅላላና ልዩ ዕውቀት፣ እንዲሁም ከግብርና ቀረጥ ጋር በተገናኘ ጥፋት ካልፈፀሙ ሰዎች መካከል ተመርጠው ይሰየማሉ።"

፲፫/ ከአዋጁ አንቀጽ ፩፻፲፬ ንዑስ አንቀጽ /፬/ ውስጥ "ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፩፻፲፫/፫/ ከተዘረዘሩት መካከል" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፫/ ከተዘረዘሩት መካከል" በሚለው ተተክቷል።

፲፬/ የአዋጁ አንቀጽ ፩፻፲፬ ንዑስ አንቀጽ /፮/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፮/ ተተክቷል፤



3/ The Tax Authority's officer shall be held responsible for any damage caused to a taxpayer by delaying without any good cause, the performance of his/her duty. Such officer in addition to being held liable for the damage, shall, upon conviction, be punished with imprisonment for a term of not less than one year and not more than two years."

10/ Sub article (1) of Article 112 of the Proclamation is repealed and replaced by the following new sub article (1):

"1/ Any party dissatisfied with a decision of the Appeal Commission, on the ground that it is erroneous on any matter of law, may appeal to the competent court of appeal within 30 days from the date of receipt of the written decision of the Appeal Commission."

11/ Sub article (4) of Article 112 of the Proclamation is repealed.

12/ Sub article (1) of Article 114 of the Proclamation is repealed and replaced by the following new sub article (1):

"1/ Members of Appeal Commission at every level shall be appointed from among persons, including representatives of business communities, having good reputation, acceptability, general and professional knowledge, and who have not committed any offence in connection with tax and tax administration."

13/ The phrase "by appropriate entities listed under Article 113(3) above" is repealed and replaced by the phrase "by the appropriate organs from among persons referred to in sub article (3) of this Article."

14/ Sub article (6) of Article 114 of the Proclamation is repealed and replaced by the following new sub article (6):

"፮/ የማንኛውም የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አባል የአገልግሎት ዘመን ለሁለት ዓመታት ጊዜ ይሆናል። በይግባኝ ጉባኤ ወይም በጉባዔው ችሎት በሊቀመን በርነት እንዲያገለግል የተመረጠ ሰው የሥራ ዘመን ለሁለት ዓመት ወይም በምትክነት የተመረጠ ሲሆን የተካው ሰው ለቀረው የሥራ ጊዜ ይሆናል። ከሁለት ዓመት በላይ የሥራ የጉባዔ አባል እንዳስፈላጊነቱ በድጋሚ ሊመረጥ ይችላል።"

፫. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥር ፩ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

"6/ The term of office of a member of an Appeal Commission shall be for two years. A member appointed to chair an Appeal Commission or a panel of the Commission shall serve in that capacity for two years or the remaining period of that other member's term if he is a substitute. Where necessary, any member of an Appeal Commission may be assigned for another term of office."

4. **Effective Date**

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 9th day of January, 2009**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**